# አለቀ አከተመ

ብአዴን ተብሎ ፣ ለወያኔ ያደረው
አማራን እያየ ፣ በግፍ ያስመተረው
ስሙ ቢቀየርም ፣ የማይቀየረው
ያጋሰሰ ጥርቅም ፣ ዘመን ያስቆጠረው
ያድር ባዮች ሽንጎ ፣ ለጉድ የፈጠረው
ዛሬም በኦዴፓ ፣ የሚያሽከረክረው
ሰው ጠፋ ወይ ባገር ፣ የሚገፈትረው
ደም እየነገደ ፣ ዛሬም የሚጦረው ።

እዚያው ካጠገቡ ፣ ከሰሩ ሆናችሁ
አይናችሁ እያየ ፣ አልታይ ያላችሁ
ከስልጣኑም መድረክ ፣ እራሽን ነፍጓችሁ
አይደለም ከገጠር ፣ ከመሃል ከተማ ፣
ሲያፈናቅላችሁ
          ኢትዮጵያ ሚኒሊክ ፣ ብቻ ስላላችሁ
          ዛሬም ካብይ ጋር ፣ ታራግባላችሁ
          እያሽመደመደ ፣ እያስገባላችሁ ።

ጥንት እንደነበረው ፣ ዘመነ ወያኔ
ቢሾም ካንድ ጎሳ ፣ ለውጥ አላየም አይኔ
የነገዱም ቡድን ፣ ዘንድሮም ምስለኔ
ሁሌም አጎንብሶ ፣ ለመጣ አረመኔ
መነገጃ ሆኗል ፣ አማራው ወገኔ
          አታጋይ ያለው ቡድን ፣ ሆነና ሽማኔ
          እንዴት ገፍቶ ይውጣ ፣ ዛሬም በጭካኔ ።

መውጣት እንዲያስችለው ፣ አቀበት ዳገቱን
የአማራን ስስ ብልት ፣ ኢትዮጵያዊነቱን
የሚያኮላሸውን ፣ የሚያፈስ ሃሞቱን
ሚኒሊክ ተፈሪ ፣ ነገስታት የጥንቱን
እየተረከለት ፣ ማንነት ኩራቱን
በደንብ በተጠና ፣ አዘጋጅቶ ስልቱን
ወዳጄ ነው እንዲል ፣ ምንደኛ ጠላቱን
አባብሎ በዘዴ ፣ መቀንጠስ ማጅራቱን ።

በተግባሩ ሌላ ፣ ባፉ ማር ሲናገር
አስመስሎ መቅረብ ፣ ስልጡን በማጭበርበር
ይህንን ይመስላል ፣ የአብይ መደመር
ያቀፈ አስመስሎ ፣ እያራቀ መቅበር
አመልና ጭራ ፣ ይታያል እያደር ።

በመንደር በጎሳ ፣ የተጠራቀመ
ልክ እንደ ወያኔ ፣ በፅኑ የታመመ
ገና ከጅምሩ ፣ ኮምጥጦ ያልጣመ
እንዲህ በመወስለት ፣ ዘልቆ ከከረመ
ስሩን ከሰደደ ፣ ደልድሎ ከቆመ
          የኢትዮጵያ ጉዳይ ፣ አለቀ አከተመ
          ነገ የምናየው ነው ፣ አብይ በለው ለማ ፣
          ምን እንደተለመ ።

ታዛቢው

February 14, 2019